# ፅድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም ከከፋት ደግነት ሳይሻል ኣይቀርም

*በሚኪኤል ምሩፅ 12-07-17*

ኣሁን ኣሁን በተለያዩ የኣገራችን ክፍሎች እየተፈጠረ ያለው ሁኔታ ዝምታ ሊቸረው ኣይገባም።

እንደ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በየወቅቱ እየተከሰቱ ስላሉ ጉዳዮች ለኣንድ ቀን እንኳን ሳላስብ ያለፍኩበት ግዜ የለም። ኣገራችን ላለፉት 27 ዓመታት የተመዘገበ እድገት ስናይ ኢትዮጵያ የሚል ስያሜ ከተሰጣት ግዜ ኣንስቶ የደርግ ስርዓት እስከተገረሰሰበት ወቅት ድረስ ከቶውንም ያልታየ እድገት የተመዘገበባት፣ ሰላምና መረጋጋት ለርሷ ተርፎ ለጎረቤት ኣገሮች በማካፈል ፍፁም የተረጋጋ የኑሮ ሁኔታ የተረጋገጠበት ቀጠና እንዲኖር ያስቻለችና የወደፊት ብሩህ ተስፋ የምታማትር ኣገር መሆንዋ ከዜጎችዋ ኣልፎ በውጭ ኣገር ዜጎች እና ዓለም ኣቀፍ ተቋማት የተመሰከረ ኣገር ያወቀው ፀሃይ የሞቀው ሓቅ ነው።

ለዚህ ስኬት ዋናው ምክንያት እና ባለቤት ማነው ቢባል ለኣንዱ ወይም ለሌላው ተነጥሎ የሚሰጥ ኣይደለም። በመፈቃቀር በመከባበርና በኣንድነት ኣምነን ሁላችንም ለለውጥ ስለተጋን ነው። ህብረ-ብሄራዊ የፌደራል ስርዓታችን በብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መካከል በፈቃደኝነትና በመፈቃቀር የተመሰረተ ኣንድነት ያላበሰን፤ ኣገራችን በኢኮኖሚ፣በፖለቲካና በማህበራዊ እሴቶች ከማሽቆልቆል ጎዳና ኣውጥቶ ወደ እድገትና ብልፅግና ምህዋር ያስገባን፤ እንዲሁም ማንኛውም ዜጋ በየትኛውም የኣገሪቱ ክፍል በነፃነት ሊኖር፣ ሊንቀሳቀስና ሰርቶ ሊበላ ዕድል የሚሰጥ መሆኑን ግልፅ ነው።

መሪዎቻችን እንዳለፉት ነገስታትና መንግስታት እኛ ከእግዚኣብሄር የተላክን ለንግስና የታጨን ነን እና ስገዱልን ኣላሉም።ኣልያም ወታደራዊ ስልጣን ኖሯቸው በመፈንቅለ መንግስት ወደ ስልጣን የተቆናጠጡም ኣይደሉም። በወቅቱ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ማንነታቸውን ተቀምተው መኖር ባለመቻላቸው፣ በየኣስፋልቱ የሰው ልጅ ያለሃጥያቱ በጥይት ግንባሩ ተመትቶ ደሙ በከንቱ ሲፈስ፣ የወለደች እናት እንኳን ሆድ ኣላስችል ብሏት በልጆችዋ ሞት ማዘን ስትከለከል ማየት ሰልችትዋቸው፤ ከዚህም በከፋ መልኩ ልጆችዋ ለተገደሉበት ጥይት ለመክፈል የምትገደድበት ሁኔታን ኣማርረው ላንዴና ለመጨረሻ ህይወት ከፍለው የዜጎቻቸው ህይወት ለማትረፍ ህዝባዊ ኣስተሳሰብ ኣንግበው የትጥቅ ትግል በማካሄድ ስርዓቱን ለመቀልበስ በቅርብ ርቀት ተጋፍጠው፣ ታግለውና ኣስታግለው የኢትዮጵያን ህዝብ ከደርግ መንጋጋ ነፃ ያወጡና በኣገሪቱ የነበረ ጨቋኝ ስርዓት መቀመቅ ኣውርደው ለዚህ ድል ያደረሱን ናቸው።

ጨቋኝ ስርዓቱ ካስወገዱም ቢሆን እኛ ነን የታገልነው ስልጣኑ ለኛ ነው የሚገባን ሳይሉ ከኣገር ውስጥም ከውጭም የነበሩ ዜጎች፣ እነሱንም ጭምር ስያሰቃዩና ሲወጉ የነበሩ የተደራጁ ሃይሎች ሳይቀሩ በፖለቲካው እንዲሳተፉ በማድረግ ወደ ስልጣን መውጣት የሚቻለው በምርጫና በምርጫ ብቻ ነው ብለው ኣዋጆች፣ ኣሰራሮች፣ ደንቦችና መመርያዎች በማበጀት በትልቁም በኣገራችን ለሚተገበሩ ሕጎች ገዢ የሆነ ህገ-መንግስት ኣርቅቀው በማፅደቅ ህዝባዊነታቸውን ያሳዩበት ታሪክም የቅርብ ትውስታችን ነው።

ታድያ እንዲህ የኣገራችን እድገት ገና በሁለት እግሩ ኣደላድሎ ባልረገጠበት፣ ዴሞክራሲ ዳዴ እያለና እየተንፏቀቀ ባለበት ምድር ኣሁን ምን ተገኝቶ ይሆን እርስ በርስ መናቆሩ እያየለ የመጣው? ኣንዱን ለሌላኛው ለምን ይጠራጠራል? ኬቱ የቱ ተሻለና ምርጫችን ማውደምና ማቃጠል፣ መሰረተ-ልማቶችን ማፈራረስ ሆነ?

በርግጥ ኣሁን ያለው ስርዓት ለኣገራችን በርካታ ትሩፋቶች ያስገኘ ነው። እንደ መዓዝን ድንጋይ ከሚታዩ ለወደፊትም ማንኛውም ኣካል ሊሸራቸው የማይችል ለመጥቀስ ያክል የብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሉኣላዊነትና ኣንድነት፣ የቋንቋ የሃይማኖት እኩልነት፣ ሃሳብን በነፃ ማንሸራሸር የሚሉ በሕገ-መንግስቱ የተደገፉ ናቸው።

ይሁንና ይህን እንደወርቅ የነጠረ ሕገ-መንግስት በህዝብ ተኣማኒነት ያላቸው ሕጎችና ፖሊሲዎች በስትክክል በማስፈፀም ረገድ ምንም እንከን የለውም ማለት ግን ከቶውንም ኣያስብልም።ታድያ ስህተቶች በተፈጠሩ ልክ ድንጋይ ብንወራወር፣የእሳት ፍም ብናቀጣጥል፣ በስንት መከራ ለፍተን ያነፅነው ዕድገትና መሰረተ ልማት ብናፈራርስ በእሳት ብናጋይ ምነው ጥያቄያችን ዘነጋነው?

ከተለያዩ የሕ/ሰብ ክፍሎች በተለያዩ መድረኮች ከሚነሱ ጥያቄዎች እንደምንረዳው በየቀጠናው ለሚነሱ ረብሻዎች ምክንያት ተደርገው ሲጠቀሱ እንደምንሰማው በኣካባብያችን እድገት ኣልተረጋገጠም፣ መሰረተ ልማት ተጓደለብን፣መልካም ኣስተዳደር

ኣጣን፣ የስራ እድል ተነፈግን የሚሉ ዋናዎቹ ናቸው። ታድያ እሳት በእሳት ማጥፋት ከየት የተማርነው ተሞኩሮ ነው። በሰላማዊ መንገድ መጠየቅና መቃወም እያለ ኣገር ማፈራረሱ ኣንዱን ለሌላው መጥላቱና ከመጥላትም ኣልፎ መገዳደሉና መጎዳዳቱ ለማን ይበጃል?

በርግጥ የመሰረተ ልማት መጓደል፣የፍትህ እጦት እና የመልካም ኣስተዳደር መጓደል የጫረው ሁከት/ብጥብጥ/ ከሆነ ለምን ቀድሞ የተሰሩልንን መሰረተ ልማቶች እናፈራርሳለን? ጥያቄኣችን ባጭሩ እንዲመለስ? ወይስ ችግሩን ተባብሶ ጥያቄውም እንዲቀጣጠል? ተማሪዎች ተረጋግተው እንዳይማሩ ማወክ ስልጣኔ ወይንስ ኋላቀርነት? ወገን ልብ እንበል "ኣንዱ ገራገር ሌላው በተንኮል" ሳይሆን ኣይቀርም ነገሩ።

በተለያዩ ኣጋጣሚዎች ኣንገታቸውን ኣቀርቅረው የዋሁ ህዝብ እንደጅረት ወንዝ እነሱ በፈለጉትና ዒላማቸውን በምያሳኩበት መንገድ እየገሩት እንዳይሆን ማስተዋል ይበጃል። ያስተዋለ ብዙ ርቀት ይጓዛል እንደሚባል በሁሉም እንቅስቃሴዎቻችን ምክንያታዊ እንሁን።በእለት ተእለት ንሮኣችን ለምንወስዳቸው እርምጃዎች የመጨረሻ ውጤት ምን እንደሚሆን እያሰብን እንከውን። የምንወስደው እርምጃ ለምን ስለምን በምን ምክንያት ለማን መሆኑን እናሰላስል፡፡

ኣንዳንዴ ሳናስበው በኣቅራብያችን ባሉ ኣንዳንድ ግብረገብነት የጎደላቸውና ከኣሰራር ውጭ እየሆኑ ህዝብን እንዲያማርር የሚጥሩ ኣመራሮች ተማርረን ወዳልተፈለገ ብጥብጥ መግባት ጉዳቱ ለሁሉም ነው።

እንደኛ ላሉ በኢኮኖሚ ገና ያልጠነከሩ ኣገሮች ከምንም በላይ ሰላምና የተረጋጋ ቀጠና እንዲኖራቸው መፍቀድ ትልቅ ዋስትና ነው። የሰላም ዋስትና የሌላት ኣገር የትም መድረስ ኣትችልም።ህልሟ ማሳካት ይቅር የስኬቱ ኣጋማሽ ለመድረስ እንኳን ሊያጋጥም የሚችል የዜጎች እልቂት ማንኛውም ሰው ትሪያንጉለይት ማድረግ ኣያስፈልገውም። በሁሉም ኣጀንዳ ዘው ብለን ከመግባት ስለኣጀንዳውና የመጨረሻው ግብ ራሳችንን እንጠይቅ። መጥፎ ዒላማ ያነገቡ ኣካላት በኣሳቻ ሰዓትና በኣሳቻ ተግባር ተሰንቅረው ተግባራቸውን ሊከውኑ ይዳዳሉ። ስርዓት ማፍረስ ሕግ-ኣልበኝነትን ያሰፍናል። እነኣጃግሬ ፌደራሊዝምን ይኮንናሉ፤ የህዝቦች ኣንድነትን ያጥላላሉ፤ ኣንተ ከእገሌ ትበልጣለህ እገሌ እየመራህነው የሚል የምሬት ዘፈን ሁሌም ይቆዝማሉ።

ራሳቸውን ችለው መራመድ ኣይችሉም ታድያ እንደኣማራጭ የሚወስዱት በተዳከመ ኣቅማቸው እዚህም እዝያም ቀዳዳ እየፈለጉ ቀዳዳዉን እንዲሞላ ሳይሆን በዛን ክፍተት ገብተው ህዝብን ማደናገር፣ ማተራመስ የቀቢፀ ተስፋ ዓላማ ሰንቀው ህይወታቸውን ያራዝማሉ። ይህን ሁሉ ብጥብጥ በቅርበት ለመምራት ወኔና ሃሞት ስለሌላቸውም በሰው ኣገር ተሰደው በነጮች ትርፍራፊ እየደለቡ። ህዝብን ከህዝብ የማጋጨት ተግባራቸውን ከውጭ ኣገር በርቀት ተቀምጠው ኣገርውስጥ እንዳሉ በማስመሰል በማህበራዊ ሚድያ መቀስቀስ ትልቁ ስልታቸው ነው።

ስለዚህም ህብረ-ብሄራዊ ፌደራሊዝም ለኣገራችን ትክክለኛው የልብስ ቅድ ነው።ይህንኑ ልብስ ኣስተካክሎ መልበስ ከማንኛውም ዜጋና ኣመራር ይጠበቃል። ኣለም እንደ ኣንድ ማእድ ለማድረግ በሚታሰብበት ሰዓት፣ ኣፍሪካን ተዋህደንና ተዋደን በኢኮኖሚም በኣስተሳሰብም ኣቅም ፈጥረን ኣህጉራችን ከፍ ለማድረግ በምንሯሯጥበት ወቅት መከፋፈል ለምን? እንኳንስ ዘንቦብሽ ድሮውም ጤዛ ነሽ የኣበው ተረት እንዳይሳለቅብን መጠንቀቅ ለሁሉም ይበጃል።

***ማንም የማንም ጠላት ኣይደለም*** ለሁላችን የሚያዳክም ጠላት ግን ድህነት፣ኋላ ቀርነት፣ ድንቁርናና የእርስበርስ መናቆር ብቻ ናቸው። ለኔ እንደሚገባኝ ከሆነ ኢትዮጵያዊነት ፍቅር ነው፤መከባበር ነው፤ መደጋገፍና መተዛዘን ነው።

ኣንድ ታሪክ ላውሳችሁ በህውሐት ትግል ወቅት ማንኛውም የህዋሓት ታጋይ ከደርግ ወታደራዊ ኣገዛዝ ጦር ሲዋጋ በጣም ብዙ ሰዓታትን የወሰዱ ጦርነቶች ተካሂደው የታጋዩን ጓድ በጥይት የገደለ የደርግ ሰራዊት እንኳን እጁን ከሰጠ፣ በዛች ቅፅበት የጓዱን መሞት ዓላማውን ሳያስተው እጁን ለሰጠ የደርግ ሰራዊት በክብር ተቀብሎ የሚያቆይና የሚያስተምር፤ ኣስተምሮም በምርጫው ሊታገል ኣልያም በክብር ወደፈለገበት እንዲሸኝ ያደረገ ነበር። ምክንያቱም ሰው መግደል የመጨረሻ ኣማራጭ እንጅ ለሚያልማት ኢትዮጵያ እንደማይበጅ ጠንቅቆ ያውቅ ስለነበር ነው።ኣላስፈላጊ ግብ ማስቀረት የሚቻለው ህዝብን በመጨረስ/በማንጠፍ/ ሳይሆን ኣመለካከቱን በመቀየር ነው። ሰውና ኣመለካከቱ ሁለት ናቸው።

ታድያ ይህን ታሪክ ለምን ኣነሳህ ማለታችሁ ኣይቀርም። ነገሩ እንዲህ ነው፡- ማንኛውም ኣመራር ከሕ/ሰብ ነው የሚወጣው ከሰማየሰማያት የሚወርድ ኣካል የለም። መሪዎች ብፁኣን ኣይደሉም ልክ ሁላችንም በእለት ተእለት ተግባራችን ብዙ ትናንሽና ትላልቅ ስህተቶች እንደምንፈፅም ሁሉ እነሱም ሁሌ በስትክክል ሊጓዙ ኣይችሉም። ታድያ ለዚህ መህትሄ የሚሆን በትልቁ መፅሓፋችን/ሕገ-መንግስት/ የተቀመጡ መፍትሄዎች ስላሉ በመስመር ተጉዞ መፍትሔ ማበጀት እንጂ መናቆር፣ ማውደም፣ ማቀጣጠል በየትኛውም መልኩና በየትኛውም ሰዓት መፍትሔ ሊሆን ኣይችልም።

ሌላው ልብ ማለት ያለብን ኣጀንዳ በረብሻ፣ በጦርነት እና በሁከት ኣሸናፊም ተሸናፊም ሊኖር ኣይችልም። ይህም እሩቅ ሳንጓዝ ከርዋንዳ ብሩንዲ፣ ሶማልያና ሴራልዮን የመሳሰሉ ኣገሮች ቀደም ሲል ከነበሩ የብሄርና የጎሳ ጦርነቶች የዜጎቻቸው ህይወት መቀጠፍና በሚልዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻቸው ያለምክንያት እጅ እግራቸው መቆረጥ፣ ሴቶች ጡታቸው መቆረጥ በህዝቡ ዘንድ

የነበረ የእርስበርስ ጥላቻና መናቆር መማር ግድ ይለናል። በሁከትና በግርግር ችግሮች ኣይፈቱም። የኣንድም ዜጋ በግርግር ለሚፈጠር ህልፈተ ህይወት መፍቀድ የለብንም። የጦርነት ሶቆቃ ባለፈው ስርዓት ቀምሰናል በዚሁ ይብቃን። ኣገራችን ኢትዮጵያ ለማበልፀግና በኢኮኖሚ ወደ ከፍታ ለማድረስ ልዩነታችን ውበታችን ነው ብለን ለስራ እንትጋ።

*None of us is as smart as all of us*

ቸር እንሰንብት

መልካሙን ሁሉ ለኣገራችን እመኛለሁ